በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ
ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ



# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከዲሴምበር 21-31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

## እንዲሁም ከ1-10 እና ከ11-20 ጃንዋሪ 2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

ጃንዋሪ 1/1/2024
አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

*ርዕስ* *ገፅ*

እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ - 1 -
ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ - 2 -
ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ........ - 2 -
ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 2 -
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 3 -
ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 3 -
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 4 -
ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 ........ - 4 -
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 4 -
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ - 5 -
ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 1-10, 2024 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ........ - 6 -
ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 6 -
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ ........ - 6 -
ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 7 -
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 7 -
እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........ - 8 -



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

በዲሴምበር ወር የመጨረሻዎቹ አስራ አንድ ቀናት አብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅና ፀሐያማ የአየር ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል፡፡ ነገር ግ  አልፎ አልፎ ከተጠናከሩ የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት በበጋ ወቅት ዝናብ የማያገኙት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ  ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበ ሲሆን፤ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ጣቢያዎች መካከል በአርባምንጭ 46.8፣ በጂንካ 42.1፣ በጭራ 45.2፣ በአሊያ 36.0 እንዲሁም በሚኤሶ 33.0 በሚ.ሜ. ናቸው፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ እንዲሁም ጥቂት የሲዳማ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል የባሌ፣ የምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና ዞኖች እንዲሁም የምዕራብ ሀረርጌ ላይ ከ5-57 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-4 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኢታንግ ልዩ ዞን እና ከአኙዋክ በስተቀር ሁሉም የጋምቤላ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ከቄለም ወለጋ፣ ኢሉ አባቦራ፣ ጅማ፣ የምዕራብ ሸዋ እና ምዕራብ ሀረርጌ ፣ የባሌና ጉጂ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል የማኦኮሞ ልዩ ወረዳ ዞን፤ የምስራቅ ጎጃም ፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ እንዲሁም የሲዳማ ደቡባዊው ክፍል ላይ መደበኛና ከመደበኛው በላይ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ፡፡


በሌላ በኩል የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና መካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ውስጥ ከ 5 ዲግሪ ሴልሸየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023
ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023
ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረዉ
የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የዲሴምበር የሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስተዋለ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ እንደነበረ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት ለጥቂት ቀናት ተስተውሏል፡፡ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

በዲሴምበር ሶስተኛ አስራ አንድ ቀናት በታችኛው ኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛዉ ባሮ አኮቦ፣ በጥቂት የመካከለኛው አዋሽና የላይኛው ዋቤ ሸበሌ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸዉ፡፡ ይህም ሁኔታ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ለከርሰ ምድርና ለገጸ ምድር ውሃ አዎንታዊ አሰተዋጽኦ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል በአብዛኛው አዋሽ፣ አባይ፣ አፋር ደናክል፣ ገናሌዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌ፣ ተከዜ እና ኦጋዴን ተፋሰሶች ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሆነው ቆይተዋል፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 21 እስከ 31/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሃያማውና ነፋሻማው አየር ሁኔታ ቀጣይነት እንደሚኖረው አሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡባዊና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ እና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7 )፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ፤ በመካከለኛዉና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በምስራቅ አማራ፤ መካከለኛውና በምስራቅ የሀሪቱ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)፡፡


በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ የጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂና የቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ የመካከለኛዉ ኢትዮጵያ ክልል፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 7)፡፡ በተጨማሪም ከአማራ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፤ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች እንዲሁም የሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ የሰሜን ሸዋ (ሰላሌ)፣ የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ የምስራቅና የምዕራብ ሀረርጌ እንዲሁም ድሬዳዋና ሃረሪ፤ የመካከለኛዉ፣ የምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች እንዲሁም ከአፋር ክልል ዞን 2፣ 4፣ 3 እና 5 ቀላል መጠን ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)። በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናትም በምስራቅ አማራ፤ በመካከለኛው እና በምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚስተዋል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 1-10, 2024 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 1-10, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ


## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ የሁለተኛው አስር ቀናት የበጋው ደረቅ፤ ፀሀያማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ የሚስተዋል ቢሆንም፤ በጸሀይ ኃይል ታግዘው ከሚፈጠሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በደቡብና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ክምችት እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 8)፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የሀገራችን ሶማሌ ክልል ደቡባዊ ክፍል፣ ጉጂ፣ ቦረና፣ የሲዳማ ክልል፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራል (ካርታ 8)፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

Rainfall performance (mm) for 11-20 Jan 2024




ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11-20፣ 2024 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረው የአየር ሁኔታ በአሁኑ ወቅት በመከናወን ላይ ለሚገኘው የድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በሌላም በኩል በተለይም በደቡብ አጋማሽና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው እርጥበት ዘግይተው ለተዘሩ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱት ለደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ለሚያከናውኑት የእንስሳት ልማትም ሆነ ለሰብሎችና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ፣ በመካከለኛው እና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪ የበልግ ወቅትን ቀድመው



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በላይኛውና በመካከለኛው ኦሞጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት የላይኛውና የመካከለኛ አባይ፣ በጥቂት የላይኛው ገናሌዳዋ፣ በባሮ አኮቦ፣ በጥቂት የአፋር ደናክል እና በላይኛውና በመካከለኛው ተከዜ እንዲሁም በመካከለኛው አዋሽ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ያገኛሉ፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et